4-3/104/10

7 መጋቢት 2010

የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ለሚፈጸምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ

በያሉበት

ጉዳዩ፡- ኢንጂን ቀይረው ወደ አገር የሚገቡ ተሽከርካሪዎችን ይመለከታል

የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በቁጥር አቃጉ 01/አ51/238 በ14/06/2010 ዓ.ም. በፃፈው ደብዳቤ በቅ/ጽ/ቤታቸው ተመዝግበው ወደ አገር ውስጥ ከገቡ ተሽከርካሪዎች መካከል የሻንሲ ቁጥር መነሻቸው NZE141 የሆነ Toyota corolla ተሽከርካሪዎች በተሽከርካሪዎቹ VIN እና ሞደል መሠረት ከMOENCO ካታሎግ እና ከኢንተርኔት በተገኘ መረጃ የተሽከርካሪዎቹ ሲሲ 1500CC እንደነበረ የተረጋገጠ መሆኑን በመግለፅ ነገር ግን በቅ/ጽ/ቤቱ የፍተሻ ባለሙያ በአካል ሲፈተሽ የተገኘው 1298CC በመሆኑ የተሽከርካሪው ሞተር (engine) መቀየሩ ተጠቃሚዎቹን ሊጎዳ ስለሚችል ወይም ተሽከርካሪው ከጉምሩክ ከወጣ በኋላ የራሱን ኢንጂን (1500cc) ሊቀየርለት የሚችልበት እድል ስላለ በመንግስት ገቢ ላይ አሉታዊ ተፅኖ ሊኖረው ስለሚችል በእኛ በኩል ታይቶ ማብራሪያ እንዲንሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡

ይህንንም መነሻ በማድረግ ተሽከርካሪዎቹ ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡበት ጊዜ በጉምሩክ ባለሞያ በተግባር የሚገኘው የሞተር አይነትና አቅም የVIN ቁጥራቸውን መሰረት በማድረግ ኢንተርኔትን ጨምሮ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ጋር ሲነጻጸር ከሚገኘው የሞተር አይነትና አቅም ልዩነት ያለው ሆኖ ሲገኝ በፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን በኩል በየትኛው የመረጃ ምንጭ መሰረት ለተጠቃሚዎች እንደሚያስተላለፍ ማብራሪያ እንድሰጡን ወይም እንደነዚህ አይነት ተሽከርካሪዎች ወደ አገር ዉስጥ ሲገቡ ለተጠቃሚዎች የሚተላለፉበት የሕግ መሰረት

ካለ እንዲገልፅልን የጠየቅን ሲሆን  ከላይ የተጠቀሱት ተሽከርካሪዎች ዓይነት በቅ/ጽ/ቤታችሁ በኩል የሚገቡ ካሉ ከተጠየቀው መስሪያ ቤት መልስ መቶ ወጥ የሆን አሰራሩን እስከምናሳውቃችሁ ድረስ ሙሉ የፍተሻ መረጃው በጥንቃቄ እየተያ። · የተሽከርካሪዎቹ ሰነድ ሳይበትን በተመጣጣኝ ዋስትና እንድታስተናግዱ እናሳስባለን።

ከሠላምታ ጋር

ጌቱ ሰገሠ

የዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ አሰራርና ድጋፍ

ዳይሬክተር

<u>ግልባጭ</u>

- ለጉምሩክ ዘርፍ
- ለሕግ ማስከበር ዘርፍ
- ለታሪፍ ምደባ አሰራርና ድጋፍ ቡድን

<u>ኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን</u>